# +++ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ +++

# የዕለት እንጀራ

፻፵ኛው

መጋቢት ፳፯ **መዝሙር ፳፪** ፳፻፩

፵ኛው የጾም ቀን

የዐቢይ ጾም እያንዳንዱ ሳምንት (እሁድ) ከጌታችንና አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርትና ስራ ጋር በተያያዘ ስም ተስጥቶት ተከፍሏል:: ይህ ሳምንት ገብር ኄር ይባላል:: ገብር ኄር በጎ ታማኝ ባሪያ ማለት ነው::

አሁንስ፥ ይላል እግዚአብሔር፥ በፍጹም ልባችሁ፥ በጾምም፥ በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ። ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ
ኢዩ፪:፲፪-

**እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም። በለመለመ መስክ ያሳድረኛል በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል። ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ። በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም በትርህና ምርኵዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል። በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ፥ ጽዋዬም የተረፈ ነው። ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፥ በእግዚአብሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።**

አምላካችሁም እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ፥ ቍጣው የዘገየ፥ ምሕረቱም የበዛ፥ ለክፋትም የተጸጸተ ነውና ወደ እርሱ ተመለሱ።
ኢዩ ፪: ፲፫

## በዚህ ዕለት ከሚታሰቡት መካከል:

ጻድቁ ተክለሃይማኖት

### እንዲያውቁት

ሆሳዕና - ሚያዝያ 4 (April 12)

### እንዲያውቁት

ስቅለት - ሚያዝያ 9 (April 17)
ትንሳኤ - ሚያዝያ 11 (April 19)